# ጥናት አንድ 2ኛ ጢሞ 1፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጸሃፊው ራሱን የሚያስተዋውቀው በእግዚአብሄር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሃዋርያ እንደሆነ ሲሆን፤ ጢሞቲዎስን ደግሞ ‹‹ተወዳጁ ልጄ›› በማለት ነው የሚናገረው፡፡
2. በቁ3 ላይ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ በትጋት ሳያቋርጥ ሌሊትና ቀን ሲጸልይለት ነው የምንመለከተው፤ በቁ 6 ላይ ደግሞ ከጌታ የተቀበለውን ስጦታውን እንዲጠቀምበት ሲያበረታታው እናያለን፡፡ ከዚህ የጳውሎስ ድርጊት የምማረው ለሰዎች ምክርና በህይወታቸው ማድረግ ስለሚገባቸው ነገር ሃሳብ ከመለገስ ጋራ አስቀድመን በጌታ ፊት በጸሎት ማቅረብ እንደሚኖርብን ያስተምረኛል፡፡
3. በጢሞቲዎስ ውስጥ የሚታየውን የእምነት ዓይነት ጳውሎስ ግብዝነት የሌለበት እምነት በማለት ይጠራዋል፡፡ ከዚህ አነጋገሩ እንደምንረዳው ግብዝነት የሌለበት እምነት ካለ በሌላ በኩል ደግሞ ግብዝነት ያለበት በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው አይነት እንዳለ ነው መረዳት የምችለው፡፡ እናቱንና አያቱን በዚህ ሥፍራ መጥቀስ የፈለገበት ምክንያት እንደሚመስለኝ ከሆነ ቤተሰብ በተለይም ይህንን ስናነብ እናቶችና አያቶች በመንፈሳዊ ህይወታችን ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አስተዋጽዖ ሲጠቁመን ይመስለኛል፡፡
4. ስጦታውን የተቀበለው በጳውሎስ እጅ መጫን ነው፣ የስጦታው ምንጭና ሰጪው እግዚአብሄር ነው፣ የተቀበለው ስጦታ ሊያቀጣጥለው የሚችለውና የሚጠበቅበት ነው፡፡ የተቀበልናቸው፡ የሃይል መንፈስ፣ የፍቅር መንፈስና ራስን የመግዛት መንፈስ ሲሆን፤ የፍርሃት መንፈስ ግን እግዚአብሄር ያልሰጠን ነገር እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ጳውሎስ ይህንን ሃሳብ ለጢሞቲዎስ ማስተላለፍ የፈለገበትው፤ በቁ8 እንደምናነበው ወንጌልን ለመናገርም ሆነ እውነትን በድፍረት ለመናገር በሚያሳየው ድፍረት ማጣት በመነሳት እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡
5. ስለጌታ መመስከር ወይም በጳውሎስ መታሰር እንዳያፍር፣ በተጨማሪም ደግሞ በእግዚአብሄር ሃይል ስለ ወንጌል መከራን እንዲቀበል ነው የሚመክረው፡፡ እግዚአብሄር ምንም ነገር ሳናደርግ እንዲሁ በጸጋው ያዳነንና ወደ ህይወት የጠራን በመሆኑና ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት የተገለጠ ስለሆነ ማናችንም ብንሆን ጢሞቲዎስንም ጨምሮ ለጌታ ለመመስከርም ሆነ ወንጌልን ለመናገር ማፈር እንደማይገባን ነው፡፡
6. ጳውሎስ የተሾመው ለወንጌል የምስራች ነጋሪነት፣ ሐዋርያ ለመሆንና የወንጌል አስተማሪ መሆን ናቸው፡፡ ጳውሎስ ከጌታ የተቀበለውን ሹመት በሥራ ላይ ማዋሉ ያተረፈለት ነገር መከራን መቀበል እንደሆነ ቁ12 ያረጋግጥልናል፡፡ ከመከራው ባሻገር ጳውሎስ የሚያየው አንድ ነገር በቁ12 ላይ ‹‹እስከዚያች ቀን›› የሚለውን የጌታን መገለጥና የሚያገኘውን ክብረ ነው የሚያስበው፡፡
7. በዚህ ክፍል ጢሞቲዎስን የሚያዘው በመጀመሪያ ከእርሱ የሰማውን ነገር የጤናማ ትምህርት ምሳሌ አድርጎ እንዲይዝና፣ ሁለተኛው ደግሞ የተሰጠውን መልካሙን አደራ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንዲጠብቅ ነው፡፡ ‹‹የተቀበልከው መልካም አደራ ሲል በ2ኛ ጢሞ 2፡2 ላይ የተቀበለውን የወንጌል ስብከት ሃላፊነት ሲሆን፤ ይህም ይህንንም አደራ መወጣት የሚችለው በውስጡ ባለው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ብቻ እንደሆነ ይነግረዋል፡፡
8. በአንድ በኩሉ ጳውሎስን ትተው የሄዱ ፊሎጎስ፣ ሄርዋጌኔስ ሲኖሩ ከጳውሎስ ጋራ የቆሙ ደጎሞ ሄኔሲፎሩና ቤተሰቦቹን እናያለን፡፡ ጢሞቲዎስን የሚመክረው ሁለተኛውን አይነት ሰዎች እንዲመስል ሲሆን ይኸውም በጀመሩት ጸንተው የሚቆሙትን እንዲመስል ነው፡፡ እንደሌሎቹ አደራውን ጥሎ ዘወር እንዳይል ጳውሎስን የያዘው ነገር በቁ12 ላይ የምናየው ያመነውን ጌታ ማንነት በሚገባ መረዳቱ ነው፡፡

# ጥናት ሁለት 2ኛ ጢሞ 2፡1-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በመጀመሪያ የተነገረው እርሱ ራሱ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ እንዲበረታ ሲሆን፤ ቀጥሎ የተሰጠው መመሪያ ደግሞ እርሱ የተቀበለውን ነገር ለሌሎች ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች አደራ እንዲሰጥ ነው፡፡ ከዚህ እኔ የምማረው በሌሎች ህይወት ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ከመሞከር አስቀድሞ የራሳችንን ህይወት በክርስቶስ ጸጋ ውስጥ ሊበረታና ሊያድግ እንደሚያስፈልግ አያለሁ፡፡
2. ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ያስተላለፈለት ንጹህና ያልተቀያየጠ ወንጌል ስለሆነ ያንንው እርሱም ያልተበረዘ ወንጌል እንዲሰብክ በማለት ነው፡፡ እኛም ብንሆን ለሌሎች የምናስተላልፈው ነገር ያልተሸቃቀጠ ትክክለኛ የወንጌል መልዕክት ሊሆን እንደሚገባው እማራለሁ፡፡
3. ክርስትናን ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚያነጻጽረው ከወታደር ጋራ ነው፡፡ ከወታደር የሚጠበቀው አንድ ነገር አዛዡን ለማስደሰት መጣር ነው፡፡ ልክ ወታደር አዛዡን ለማስደሰት እንደሚጥር እኛም ክርስቶስ ኢየሱስ የህይወታችን አለቃና መሪ የሆነ ሰዎች በህይወታችን ዘመን ሁሉ በማናቸውም ነገርና በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ የምናደርገውን ሁሉ ጌታችንን ደስ ለማሰኘት ብቻ ልንኖር እንደሚገባን እናያለን፡፡
4. በዚህ ቁጥር ላይ ደግሞ ከክርስትና ጋራ ተነጻጽሮ የምናነበው ነገር የስፖርት ውድድርን ነው፡፡ በዚህ ውድድር ላይ ስለሚሳተፈው ሰው የመነግረን ነገር ደግሞ፤ ይህ በስፖርቱ ላይ የሚሳተፈው ሰው ለማሸነፍና የድል አክሊል ለማግኘት ከፈለገ መወዳደር የሚኖርበት የውድድሩን ህግ ጠብቆ መሆን እንደሚኖርበት እንረዳለን፡፡
5. ስለወታደር የተናገረው ነገር እንደ ወታደር ትኩረታችን አዛዣችን የሆነውን ኢየሱስን ለማስደሰት መሆን እንደሚኖርበት፣ እስፖርተኛ ደግሞ የውድድሩን ህግ ጠብቆ እንደሚወዳደር፤ እኛም ስርዓት ይዘን ከእግዚአብሄር ቃል ሳናፈነግጥ መኖርን እና እንደ ገበሬ ደግሞ በታታሪነት፣ በትጋትና በትዕግሥት ህይወታችንን መኖርን እንማራለን፡፡
6. በነዚህ ቁጥሮች ላይ የጳውሎስ ወንጌል ሆኖ የተነገረው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር መሆኑና ከሙታን መነሳቱ ነው፡፡ ለመታሰሩና መከራን ለመቀበሉ ምክንያት ያደረገው ነገር ‹‹ለዚህም›› ስለሚል በቁ8 ላይ ለእርሱ ወንጌል የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን መነሳት የምስራች መናገሩ ነው፡፡ የእግዚአብሄር ቃል እንደማይታሰር መናገሩም፤ ጳውሎስ በእስር ቤት ሆኖም ቃሉን ሲናገር ከእስር ቤት ውጭ ቃሉ ይሰራ እንደነበረ በእስር ቤትም ውስጥ የሰዎችን ህይወት እንደሚለውጥና እንደሚያድን በማየቱ ምክንያት ነው፡፡
7. ጳውሎስ በመከራ የጸናው ለተመረጡት ሲል ነው፡፡ እኛም እግዚአብሄር የመረጣቸውን ወደእርሱ ሊመልስ የሚጠቀምበት መንገድ አድርጎ የመረጠን እኛን እንደሆነ ተቀብለን ሐዋርያው እንዳደረገው ሁሉ ወንጌልን በትጋትና መስዋዕትን ሁሉ በመክፈል ማዳረስ እንደሚኖርብን ያስተምረናል፡፡
8. ሐዋርያው ጢሞቲዎስን የመከረው ነገር በቁ7 ላይ ያስተማረውን ነገር ልብ እንዲልና እንዲያሰላስል ነው፡፡ ጌታ ማስተዋል እንዲሰጠን ካስፈለገ የእኛ ሃላፊነት እርሱ የሚነግረንን ነገር ልብ ማለትና ጊዜ ወስደን ማሰላሰል ይጠበቅብናል፡፡

# ጥናት ሶስት 2ኛ ጢሞ 2፡14-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጢሞቲዎስ እንዲያስጠነቅቃቸው የተነገረው ነገር በቃላት እንዳይነታረኩ ነው። ይህንንም ጳውሎስ እንዲነገራቸው አስፈላጊ ሆኖ ያገኘበት ምክንያት፤ በመጀመሪያ ደረጃ ጥቅም የሌለው ነገር ሲሆን፣ ከዚያም አልፎ ደግሞ የሚሰሙትን ሰዎችም የሚያፈርስ ነው።
2. ይህ ከንቱ ልፍለፋና በቃላት መነታረክ የሚያስከትላቸው ነገሮች፤ በለፍላፊው ሰው ህይወት ቁ16 እንደሚናገረው ከእግዚአብሄር እየራቀ ይሄዳል፣ ሰሚዎችን ደግሞ ከማነጽ ይልቅ ያፈርሳል (ቁ14)፣ በመጨረሻም በዙሪያው ወዳሉት ሰዎች ህይወትም እንደማይሽር ቁስል ይሰራጫል (17)።
3. ሐዋርያው የሚያበረታታው እንደማያፍር፣ የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ፣ እንደ ተመስከረለት ሰራተኛ አድርጎ ራሱን በእግዚአብሄር ፊት እንዲያቀርብ ነው። እነዚያ ሰዎች የሚያነታርክ፣ የሚያፈርስና ከእውነት የሚያርቅ ቃላትን የሚናገሩ ሲሆኑ፤ ጢሞቲዎስ ግን የታዘዘው እውነት የሆነውንና ሰዎችን የሚያንጸውን የህይወት ቃል ይዞ እንዲገኝ ነው።
4. ጳውሎስ የሰዎችን ስም በቀጥታ መጥቀስ ያስፈለገው ሃሰትን ትምህርት እየዘሩ ያሉ ሰዎች ስለሆኑ ከእነርሱ እንዲጠነቀቁና ትምህርታቸውን እንዳይቀበሉ በማለት ነው። የጌታን ስም ለሚጠሩ ሰዎች መለያ ሆኖ የተነገረው ነገር፤ ‹‹የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከክፋት ይራቅ›› የሚለው የተረጋገጠ እውነት ነው። የዚህን አነጋገር እውነተኛነት ‹‹ማህተም ያለበት፣ የማይነቃነቅና የእግዚአብሄር መሰረት ቆሟል።›› በማለት ይናገራል።
5. ትልቅ ቤት በማለት የሚናገረው በ1ኛ ጢሞ 3፡15 ስለምናየው ስለ እግዚአብሄር ቤተ ክርስትያን፤ በተለይም ያመነም ያላመነም የሚከማችባትን አጥብያ ቤ/ክርስትያን የሚናገር ይመስለኛል። የወርቅና የብር ምሳሌ ሆኖ መጠቀስ የሚችል በዚህ ክፍል እንደምናየው ጢሞቲዎስን ሲሆን፤ የእንጨትና የሸክላ ማለትም ሳልከበረ አገልግሎት ለዓለም ነገር የተሰጡት ቁ17 እንደሚነግረን ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ናቸው።
6. ከወጣትነት ክፉ ምኞት እንዲሸሽ፣ በንጹህ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋራ ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን እንዲከታተል፣ ከማይረባና ትርጉም የለሽ ከሆነ ክርክር እንዲርቅ። ሃጥያትን በመሸሽ ብቻ ክርስቶስን ወደ መምሰል ሊደረስ ስለማይችል፣ እንዲሁም ሮሜ 6፡13 እንደሚነግረን ‹‹ብልቶቻችሁን የክፋት መሳሪያ አድርጋችሁ ለሃጥያት አታቅርቡ…ብልቶቻችሁንም የጽድቅ መሳሪያ አድርጋችሁ ለእግዚአብሄር አቅርቡ።›› እንደሚል ከሃጥያት ስንሸሽ ወደ ጽድቅ መጠጋት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል።
7. የጌታ አገልጋይ ከሰዎች ጋራ የማይጣላ፣ ለሰው ሁሉ ገር የሆነ፣ ለማስተማር ብቃት ያለውና ትዕግሥተኛ ሊሆን ይገባዋል። ይህ አነጋገር በጳውሎስ ህይወት ተፈጻሚ ሆኗል ማለት የምንችለው ምንም እንኳን ብዙ አይነት ነገሮችን ቢሉትና ያልሆነ አሉዋልታ ቢዘሩበትም፤ በትዕግስት ከሁለቴም ሶስቴም በመልዕክት፣ በፊት ለፊትም እየመከረ፣ እየጸለየ የማቅናት ፍቅሩን የማሳየት እንጂ የጥላቻን ነገር እንዳላሳያቸው እናያለን።
8. ተቃዋሚዎቹ እውነትን ወደማወቅ ይደርሱ ዘንድ በየዋህነት የሚያቀና ዓይነት ሰው እንዲሆን ይጠበቅበታል። ይህንንም ማድረግ የሚኖርበት ምክንያት፤ ወደ አእምሯቸው ይመለሳሉ በሚልና፣ ፈቃዱን ሊያስፈጽማቸው ምርኮኛ አድርጎ ከያዛቸው ከዲያቢሎስ ወጥመድ እንዲያመልጡ በማሰብ ነው።

# ጥናት አራት 2ኛ ጢሞ 3:1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ልብ እንዲል የሚያስጠነቅቀው ነገር፤ በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚመጣ ነው። ለተዘረዘሩት 19 ነገሮች አንደኛ በመሆን በመሪነት የሰፈረው ሃሳብ ‹‹ራሳቸውን የሚወዱ›› የሚለው ሃሳብ ነው።
2. በተደጋጋሚ የተነገረው ቃል ‹‹የሚወዱ›› የሚል ነው። ሰዎች በራሳቸው ላይ እንጂ ለሌሎች ምንም ግድ እንደሌላቸው፣ የገንዘብ ፍቅርንም አስመልክቶ በምን መንገድ እንደሚገኝ ግድ ሳይሰጣቸው በሰው ላይ ተረጋግጠው ገንዘብ ማግኘት፣ ተድላን መውደድ የሚለውም፣ እግዚአብሄር ምን ያስባል ሳይሆን ራሴን ደስ ሊለኝ የሚችለው ምን ባደርግ ነው በሚል የትኛውንም ዋጋ ከፍሎ ተድላን ማግኘት የአብዛኛው ሰው ሙከራ ነው።
3. ራሳችንን ከልክ ባለፈ ሁኔታ የምንወድ ከሆነ ለእግዚአብሄርም ሆነ ለጎረቤታችን ተገቢውን ፍቅር ልንሰጥ አንችልም ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ቁ5 ላይ እንደምንመለከተው የእግዚአብሄርን መኖር የማያምኑ ከሃዲዎች ሳይሆኑ፣ የእግዚአብሄርን ሃይል የካዱ ሆነው እንዲሁ ሃይማኖተኛነትን የሚለማመዱ ምናልባትም በቤተ ክርስትያን ውስጥ የሚመላለሱና የሚያገለግሉም ሊሆኑ እንደሚችሉ እገምታለሁ።
4. ትክክለኛ ክርስትያን ተድላና ደስታ አያውቀውም ማለት ሳይሆን በፊሊ 4 ውስጥ ጳውሎስ እንደሚናገረው የአማኝ ደስታው በጌታ የተመሰረተ ሊሆን ሲገባው፤ እነዚህ ሰዎች ግን ተድላቸው በእግዚአብሄር መሆኑ ቀርቶ በሌላ ነገር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ሲጠቁመን ነው። ይህ ማለት ውጫዊ ብቻ የሆነ ሃይማኖተኛነትን የሚያሳዩ እንጂ እውነተኛ የሆነው ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚሰራው የደህንነት ሥራ በህይወታቸው ያልተለማመዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
5. ቁ1-5 ያለው ስለ ሰዎቹ ባህርይና ማንነታቸው የሚናገር ሲሆን፤ ቁ6-9 ደግሞ እነዚህ ሰዎች ስለሚፈጽሙትና በሌሎች ላይ ስላላቸው ተጽዕኖ የሚናገር ክፍል ነው። በየቤቱ ሾልከው እየገቡ መንፈሰ ደካማ ሴቶችን ያጠምዳሉ። አእምሯቸው የጠፋባቸው፣ ከእምነት የተጣሉና፣ እውነትን የሚቃወሙ በማለት ይናገራቸዋል።
6. ‹‹አንተ ግን በማለት ጳውሎስ ጢሞቲዎስን እያነጻጸረ ያለው በቁ1-9 ላይ ባህርያቸውንና ማንነታቸውን ከዘረዘራቸው ሰዎች ጋራ ነው። አካባቢው እግዚአብሄርን የሚያሳዝ ዓይነት ቢኖር እንኳን በጳውሎስ ህይወት ያየውናና ከእርሱ የተማረውን በማሰብ በዚያ ምሳሌነት የራሱን ህይወት እንዲመራ ሲነግረው እንደሚሆን እገምታለሁ። እግዚአብሄርን መስሎ በጽድቅና በቅድስና መኖር ምን ጊዜም ቢሆን የሚያስከፍለው መስዋዕትነት እንዳለና በዚያ ሰው ህይወት ስደት ማምጣቱ እንደማይቀር እንደሚናገር ነው የምረዳው።
7. ሁል ጊዜ ቅዱሳት መጻህፍት ወይም የእግዚአብሄርን ቃል የእግዚአብሄር መንፈስ እንዳለባቸው ይነግረናል። ቃሉ ለማስተማር፣ ለመገሰጽ፣ ለማቅናትና፣ በጽድቅ መንገድ ለመምከር መጠቀም እንደምንችል እናያለን።
8. እነዚህ ሰዎች ክፉዎች፣ አታላዮች፣ ስተው የሚያስቱ፣ በክፋታቸው እየጨመሩ የሚሄዱ ዓይነት ሰዎች ሲሆኑ፤ ጳውሎስ ግን የሚመክረው እርሱ በተማረውና በተረዳው እውነት እንዲጸና ነው። ጢሞቲዎስ የተመከረው በተማራቸው ነገሮች ብቻ እንዲጸና ሳይሆን፤ ተምሮት ውስጡ በገባና በተረዳው (convinced) በሆነበት ነገር እንዲጸና ነው።
9. እያንዳንዱ የራሱን አስተያየት እንዲናገር ጊዜ ይሰጥ።

# ጥናት አምስት 2ኛ ጢሞ 4:1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የጳውሎስ ትዕዛዝ ጥብቅና ትኩረት ሊሰጠው እንደፈለገ የሚያስገነዝበን ነገር በቁ1 ላይ የተናገረው አነጋገር ነው።
2. በሁለት ቃላት ብቻ ብናገር ማስተማር፣ ማቅናት፣ መገሰጽና፣ ማበረታታት ሁሉ ቃሉ የሚሰራቸው ነገሮች ስለሆኑ ‹‹ቃሉን ተጠቀም›› እላለሁ። ጢሞቲዎስ ቃሉን መጠቀም የሚኖርበት፤ ቁ3 እንደሚናገረው እየቆየ በሄደ ቁጥር ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል በፍርሃትና በአክብሮት የማይቀበሉበት ሰዓት ስለሚመጣ ያለውን እድል አሁኑኑ እንዲጠቀም ነው።
3. እነዚህ ሰዎች ትክክለኛውን ትምህርት አይቀበሉም፣ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን የሚናገሩትን ዓይነት አስተማሪዎች ይሰበስባሉ፣ እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፣ ወደ ተረት ዘወር ይላሉ። ጢሞቲዎስ የታዘዘው በሁኔታዎች ሁሉ የረጋ እንዲሆን፣ መከራን እንዲታገስ፣ ወንጌል ሰባኪነትን እንዲያደርግና፣ አገልግሎቱን እንዲፈጽም ነው። ይህ ያለንበት ዘመን ከማናቸውም ጊዜ በላይ የተባሉትን ዓይነት ተማሪዎችም ሆነ አስተማሪዎች እንደ አሸን የፈሉበት ሰዓት ነው።
4. ጳውሎስ የተገነዘበው ብዙም ሳይቆይ ህይወቱ ከዚህ ዓለም እንደሚያልፍ ወይም በቅርብ ጊዜ እንደሚሞት ነው። በሥጋው ለወንጌል መሞቱን ከመስዋዕትነት ለይቶ እንደማያየው፣ ህይወቱ መልካም ተጋድሎ እንደጨረሰ፣ ህይወት በውድድር ቦታ እንደሚደረግ ሩጫ እንደነበረና ከፍጻሜው እንደደረሰ ያያል፣ ሃይማኖቱን እንደጠበቀም ይነግረናል።
5. ከፊት ለፊቱ ያለውን ዘመን ብሩህና በተስፋ ተሞልቶ እንደሚጠባበቀው ነው የምናነበው። የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ጻድቁ ፈራጅ በዚያን ቀን ያስረክበዋል፣ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ ያስረክባል። ጢሞቲዎስንም የሚጨምር ተስፋ እንደሆነ የምናውቀው በእርሱ ብቻ ሳይሆን የጌታን መገለጥ ለሚናፍቁ ሁሉ ስለሆነ እርሱንም ያካትታል ማለት ነው።
6. እንዲያደርግ የታዘዛቸው፤ በተቻለው ፍጥነት ወደ እርሱ እንዲመጣ፣ ማርቆስ ለአገልግሎት ስለሚጠቅመው ይዞት እንዲያመጣው፣ በርኖሱንና ጥቅልል የብራና መጻህፍቱን ይዞለት እንዲመጣ ነው። ማርቆስን ጠቃሚ ሰው እንዲሆን ያበቃው የበርናባስ ተቀብሎ ማበረታታትና አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ነው ብዬ አምናለሁ።
7. ጳውሎስ ስለዚህ ሰው ለጢሞቲዎስ መንገር የፈለገበት ምክንያት፤ ጳውሎስን የመሰለ ሰው ብዙ ጉዳት አደረሰብኝ ካለና ጳውሎስም ሆነ ጢሞቲዎስ የሚሰብኩት መልዕክት አንድ እስከሆነ ድረስ ይህ ወጣት አገልጋይ በዚህ ሰው የበለጠ ጉዳት እንዳያገኘውና ለተቃውሞውም እንዲዘጋጅ ሲያስጠነቅቀው እንደሆነ ከቁ15 መረዳት እንችላለን።
8. ስለ ጥሮፊሞስ የተነገረን ነገር፤ ይህ ሰው ስለታመመ ከጳውሎስ ጋራ መጓዝ ስለማይችል በሚሊጢን ትቶት እንደሄደ ነው የምናውቀው። እኔ እንደሚገባኝ እግዚአብሄር ሰውን ለመፈወስ እንደሚችል ብናውቅም፣ አንዳንድ ጊዜ ግን የታመመው ሰው ምንም ዓይነት ሰው ይሁን፣ የሚጸልየውም ሰው ምንም አይነት እምነት ይኑረው፤ በዚያን ጊዜ እግዚአብሄር ለመፈወስ ካልፈለገ ማስገደድ እንደማይቻል መቀበል እንደሚኖርብን ነው የምማረው።
9. ሰዎች ሁሉ በሚፈልጋቸው ወቅት አንዳቸውም ከጎኑ እንዳልተገኙ ይናገራል፤ በዚያን ወቅት እግዚአብሄር ግን ከጎኑ ቆሞ እንዳበረታውና እንደረዳው ከአንበሳም መንጋጋ እንዳዳነው ይነግረናል። መቼም ቢሆን ዓይኖቻችን በሰዎች ላይ እንዳይሆኑና ዘወትር ሊረዳን በሚችልና በሚወደው በጌታችን ላይ እንዲሆን እንማራለን።